በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ፩

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**መስከረም ፰ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፩

## መግቢያ

- በዓመቱ የመጀመሪያ መርሐ ግብራችን ከዛሬ ጀምሮ ለጥቂት ሳምንታት የምንማረው ትምህርት መጽሐፈ ነህምያን መሠረት ያደረገውን መሪ (መሪዎች)፣ መሪነት ወይም የተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይሆናል፡፡
- በዓለማችን መጽሐፈ ነህምያን የሚያክል ስለ መሪነት ሊያስተምረን የሚችል መጽሐፍ አይገኝም፡፡
- ለመሪነት የሚያስፈልጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
- ከመጻሕፍት ሁሉ በላይ ስለ መሪነት የሚያስተምረን መጽሐፈ ነህምያ ነው፡፡ ይህን መጽሐፍ ባነበብን ቁጥር ቀስቃሽና አንቂ የሆኑ አዳዲስ መልእክቶችን እናገኝበታለን፡፡
- ዓለማችን የሚያስፈልጋትን የመሪና የአመራር ጉዳይ ሊያሳውቃት ሊገልጥላትም የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡
- አመራር (Leadeshhip) የዓለም፣ የአሜሪካ፣ የመካከለኛው ምሥራቅ፣ የቤ/ክ፣ በየቤታችን በቤተሰብ የሚታይ ችግር ነው፡፡ አመራር ከሌለ ርእይም ሆነ አቅጣጫም አይኖርም፤ ሁሉም ነገር በአመራር ሥር የሚወድቅ መሆኑ ሐቅ ነውና፡፡ ስኬትም ሆነ ውድቀት የሚመረኮዙት አመራርን ነው፡፡
- እያንዳንዱ ቤትና ክርስቲያን መሪና አመራር ያስፈልገዋል፤ መሪ ለመሆን መብቃትም ከእያንዳንዱ ክርስቲያን ይጠበቃልና፡፡
- ጥበብ የጎደለው ሥራ የሚሠሩና አመራር የሚሰጡ የብዙ መሪዎችን ውድቀት በየዕለቱ በማሠራጫዎች እየሰማለን እንገኛለን፡፡
- በዚህ ዘመን እግዚአብሔር መሪዎች ሁሉ የርሱን ፈቃድና ተልዕኮ በምድር እንዲፈጽሙለት ይፈልጋል፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፩

***መግቢያ***

- ለመሆኑ መሪዎች መሪ ሆነው ይወለዳሉ ወይስ መሪዎች ሊፈጠሩ ወይም ሊሠሩ የሚችሉ ናቸው? ወይስ መሪዎች የሚባሉት መሪ ሆነው በሚወለዱትና ሊሠሩ በቻሉት መካከል የሚገኙ ናቸው?
- እኔ መሪ ነኝ? መሪ መሆንስ ይጠበቅብኛል? ሥራዬንስ እንደ መሪ እያከናወንኩ እገኛለሁ? ወይስ ዘንግቸዋለሁ? እግዚአብሔር መሪ እንድሆን ይጠብቅብኛል? ወይስ አይጠብቅብኝም? መልካም መሪ መሆንስ የሚቻለው እንዴት ነው? በዚህ በመጽሐፈ ነህምያ ጥናታችን እነዚህ ሁሉ ጥያቄዎች ይነሱና መልስ እናገኝባቸዋለን፡፡
- እግዚአብሔር ተራ ሰዎችን ለመሪነት የሚመርጥ መሆኑ በመጽሐፈ ነህምያ የምናገኘው አንድ አስገራሚ ነገር ነው፡፡ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 11:30 ሰዓት ድረስ ወይም ከዚያም ሰዓት በላይ የተለያየ ሥራ የሚሠራ ሰውን ታላቅ ሥራን ይሠራ ዘንድ ይመርጠዋልና፡፡
- ነህምያ ቀኑን ሙሉ በሌላ የተለመደ ሥራ የሚውል ተራ ሰው ነበር እንጂ ነቢይ፣ ካህን፣ ሌዋዊ አልነበረም፡፡ ነህምያ በፋርስ ንጉሥ በአርጤክስስ ዘመነ መንግሥት የንጉሡ ጠጅ አሳላፊ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ታላቅ ሥራን ይሠራ ዘንድ መረጠው፤ የተመረጠውም የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ለማሠራት ነበር፡፡ ይህ ታላቅ ምርጫ ተወዳዳሪ በማይገኝለት ሰዓት ሥራውን ሠርቶ ለማስፈጸም ነበር፡፡
- መሪዎች የእግዚአብሔር ኃይል ወደ ሕዝቡ የሚፈስባቸው ቧንቧዎች ናቸው፡፡ እግዚአብሔር መሪዎች የርሱን ኃይል ወደ ሰዎች እንዲያደርሱለት ማስተላለፊያዎችም እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡ ጥያቄው እኔ ያንን ቧንቧ ወይም ማስተላለፊያ ነኝ ወይስ አይደለሁም፣ ዝግጁ ለመሆንስ የሚፈለግብኝ ምንድን ነው? የሚል ነው፡፡ የመጽሐፈ ነህምያ ታላቁ ተአምር - እግዚአብሔር ለታላቁ ተልዕኮ በተገቢው ሰዓት ተገቢውን ሰው መላኩ ነው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፩

**መግቢያ**

- የመጽሐፉ ታላቁ ተአምር እግዚአብሔር እኛን ለተልዕኮው በትክክለኛው ሰዓት ወደ ትክክለኛው ቦታ መላኩ እንጂ የተሠራው ቅጥር ሳይገነባ በራሱ አድጎ መገኘቱ ወይም ያልተለመደና ያልተጠበቀ ነገር መከሰቱ አይደለም፡፡ ይህም እኛ ተልዕኮአችን ወይም ጥሪያችንን የምናውቅበት ነው፡፡
- ታላቁ ተአምር እግዚአብሔር ሲጠራን ሰምተን በተገቢው ሰዓት እርምጃ መውሰዳችንና በጥሪያችን ተሰልፈን መገኘታችን ነው፡፡
- አባ ኢየሱስ ሞዓ፣ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እና ሌሎቹም አባቶች ሕዝቡ በመንፈሳዊነት፣ በትምህርት፣ በዕውቀት ማደግ ሲያስፈልገው የሚገባውን በማቅረብ ያበቁት ነበሩ፡፡ ይህም ብርሃን እስከዛሬ ድረስ ያበራል፡፡ ተአምሩ ትክክለኛው ሰው በትክክለኛው ጊዜ መጥቶ ትክክለኛውን ሥራ በእግዚአብሔር ኃይል መሥራቱ ነው፡፡ ይህም እውነተኛ ተአምር ነው፡፡
- ነህምያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየት ይገኛል ብንል፡- ከአዳም፣ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ (እስራኤል)፣ ዮሴፍ፣ ተነስተን እስራኤል በግብጽ በባርነት የኖሩበትን 400 ዘመናት ብሎም ሙሴንና በበረሃ የተንዙበን 40 ዓመታት አልፈን፣ ኢያሱን፣፣ መሳፍንትን፣ ሳሙኤልን፣ ነገሥታትን (ሳዖል፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን) ቆጥረን ንጉሡ ሮብዓም ላይ ስንደርስ እስራኤል በሰሜን (ሰማርያ - አሥሩ ነገድ - የተበላሹ መሪዎች የነበሩበትን) እና በደቡብ (ኢየሩሳሌም - ሁለቱ ነገድ - መልካምና የተበላሹ መሪዎች የተገኙበት) መከፋፈል ላይ እንደርሳለን፡፡
- በደቡን የነበሩትም ሲበድሉ - ሲበላሹ ነቢያት ተላኩላቸው፣ ንስሐ እንዲገቡ ተነገራቸው እንቢ ቢሉ ናቡከደነፆር መጥቶ ወርሮአቸው ተማረኩ፡፡ ኢየሩሳሌምም ከተማዋ፣ ቅጥርዋ፣ ቤተ መቅደሱም ሁሉ ፈራረሱ - ወደመች፡፡ በኢየሩሳሌምም ብርቱ፣ አስተዋይ የተባሉ ሁሉ ተማርከው ደካሞቹ ብቻ ቀሩ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፩

## መግቢያ

- ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል፣ አናንያ፣ አዛርያ ሚሳኤል ወደ ባቢሎን ብሎም ወደ ፋርስ አገር ተማርከው ተወሰዱ፡፡ ነህምያም እስራኤል በምርኮ ሳሉ ተወለደ፡፡ እግዚአብሔርም ከሰባ ዓመት ምርኮ በኂላ የእስራኤልን ልጆች ወደ ምድራቸው መለሳቸው፤ አመላለሳቸውም በቅደም ተከተል ነበር፤ የመጀመሪያዎቹ ከተመለሱ በኂላ ዕዝራ ቀጥሎም ነህምያ ተመለሱ፡፡
- ነህምያ ሲመለስ ሕዝቡ ኢየሩሳሌምን፣ ቅጥርዋን፣ ቤቶችዋንና ቤተ መቅደሱን መልሰው መሥራት ጀመሩ፤ እነዚህ ሁሉ ቀድመው የፈረሱትም በፖለቲካዊ ምክንያት ነው፡፡
- ቅጥራችሁ ከፍ ብሎ ከተሠራ ማንም እንደማይደርስባችሁ በቀላሉም እንደማትጠቁ ወይም ረዓብ በውስጡ እንደነበረችበት እንደ ኢያሪኮ ቅጥር - የኢየሩሳሌምም ቅጥር ከተማይቱን ሁሉ የከበበ ታላቅ ሕንጻ ሆኖ ተሠራ፡፡
- ቅጥሩ ቀላል ሳይሆን ከተማይቱን ከማንኛውም ዓይነት አደጋ መታደግ የሚችል ቅጥር ሆኖ ስለተሠራ ወታደሮች በቅጥሩ ላይ እየተንቀሳቀሱ ከተማይቱን ይጠብቁ ነበር፡፡
- የኢየሩሳሌም ቅጥር ከፈረሰ በቀላሉ እንደገና ተመልሶ ሊሠራ የሚችልበት ዕድል አልነበረም፡፡ ከተማዋን የከበበ ቅጥር መልሶ ማሠራት በምርኮ ለኖረ ሕዝብ ከባድ ነውና፡፡
- መልሰው ለመሥራት ቢፈልጉ - ቢሞክሩም ብዙ ከልካዮችና አደናቃፊዎች ነበሩባቸውና ነህምያ እስኪመጣ ድረስ አልተሠራም፡፡
- ነህምያ አሁንም የፋርስ ንጉሥ የጠጅ አሳላፊ ነበር፡፡ የፋርስ ንጉሥ እንደ ዛሬዋ አሜሪካ ፕሬዘዳንት የዓለም ‹‹መሪ›› ነበር፣ ቤተ መንግሥታቸውም እንደ ‹‹ዋይት›› ሀውስ ነበር፡፡

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፩</u>

## <u>መግቢያ</u>

- የጠጅ አሳላፊነት ሥራ ንጉሥ ላመነው ሰው ብቻ ዓይኑን እንደጨፈነ የሚሰጠው ኃላፊነት ነበር፡፡ ‹‹የሐካልያ ልጅ የነህምያ ቃል። በሀያኛው ዓመት በካሴሉ ወር እንዲህ ሆነ እኔ በሱሳ ግንብ ሳለሁ፥ ከወንድሞቼ አንዱ አናኒ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሰዎች ከይሁዳ መጡ እኔም የዳኑትን ከምርኮ የተረፉትን የአይሁድን ነገር የኢየሩሳሌምንም ነገር ጠየቅኋቸው።›› ***<u>ነህ 1፡1-2፡፡</u>***
- በዘመኑ ንጉሥ የሚወገደው በምርጫ ሳይሆን መርዛማ ነገርን በምግባቸውና በመጠጣቸው ውስጥ በመጣል ነበር፡፡ በገንዘብ እየተገዙ የመንግሥት ግልበጣ የሚያደርጉትን ሐሳብና ሕልም የሚያሳኩ ቢኖሩም ነህምያ ግን ታማኝ ነበር፡፡
- ነህምያ ንጉሥ ሲጠጣ፣ ብዙ ምስጢር ሲናገር፣ ሲሰክርም… አብሮ ቢሆንም ራሱን በመጠበቅ ደጅህን ዘግተህ ተኛ አሁን ምንም ዓይነት ውሳኔ እንዳትወስን ብሎ ደጁን የሚዘጋለት የቅርብ ወዳጅ ነበር፡፡
- ነህምያ ከሁሉም በላይ የሆኑ ምስጢሮችን የሚያውቅ ታላቅ ኃይልና ሥልጣን የነበረው ሰው ነው፤ ታዲያ በስካር ውስጥ የማይነገር ምን ነገር አለ? ሰነፎች እንዲህ ያለውን ዕድል ሲያገኙ በጉቦ ወይም በእጅ መንሻ ይታለላሉ፡፡
- ነህምያ ግን ዕድሉም ሆነ ሥልጣኑ ሳያታልለው በክብር ቦታ ላይ ሆኖ ስለ ወገኖቹ ይጨነቅና ያስብ ነበርና በኢየሩሳሌም ያሉ ወገኖቼ እንዴት ናቸው? ብሎ ጠየቀ፡፡ ሲመልሱለትም ወገኖቹ በታላቅ መከራና ስድብ ውስጥ ናቸው፣ የኢየሩሳሌምም ቅጥሮች ፈርሰዋል በሮችዋም ተቃጥለዋል አሉት፡፡ ‹‹ተመስገን እኔ በደህና ቀን ወደ ደህና ቦታ አምልጫለሁ አላለም፡፡›› ይልቁኑ ተቀምጦ አለቀሰ፣ አያሌ ቀንም አዘነ ጾመም እንዲሁ፡፡ ይህንም ለአራት ወራት ያህል ፈጸመው፡፡ ይህን ያደረገውም መሪ ከሁሉ በፊት ለሚገባው (ለሚፈለገው ነገር) ቅድሚያ ስለሚሰጥ ነው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፩

1. ***መሪ ከሁሉ በፊት አስፈላጊ ለሆኑነ ነገሮች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡***

- ነህምያ ችግሩን አይቶና ሰምቶ በዚህ ጉዳይ ምን ማድረግ ይጠበቅባኛል፣ የኔስ ድርሻ ምንድን ነው? የሚል እንጂ የእኔ ችግር አይደለም ብሎ ወይም እንዳላየም የሚያልፍ ዓይነት መሪ አልነበረም፡፡
- ነህምያ ይህን ማን አደረገው፣ ማን አፈረሰው፣ ጥፋቱ የማነው? የሚል ዓይነት ሰው አልነበረም፡፡ ምን ያስፈልጋል፣ የኔ ኃላፊነት ምንድር ነው? የሚል ነበር እንጂ፡፡ ነህምያ ለሚፈለገው ነገር ቅድሚያ ሰጥቶ ነበር፡፡ መሪ ለመሆን የምንበቃው መሪ የሚኮነውም እንደዚህ ነው!!!
- ብዙ ጊዜ ሰዎች በከፍታው የሥልጣን ቦታ ስንቀመጥ ዝቅ ብለው ያሉትን የሰው ወገኖች ማየት ወይም መቃኘት ይሳነናል፡፡ ንግሥቲቱን ባላስታውሳትም አንዱ የኔ ቢጤ ቀርቦ ብሶቱን ‹‹የምንበላው ዳቦም ሆነ የምንልሰው የምንቀምሰውም ነገር የለንም›› ብሎ ቢነግራት ንግሥቲቱም ‹‹ምን ሆነህ ነው፣ ታዲያ ዳቦ ከሌለህ ለምን ኬክ አትበላም›› አለችው የሚባለው ቀልድ መሰል የመሪዎች ማንነት ጠቋሚ መልእክት ነው፡፡
- በተለይ ክርክርን/ምክክርን - በግልጽ መነጋገርን የምናስወግድ ወይም ጥሩውንና የምንወደውን የሚያስደስተንን ጥሩውን ብቻ ንገሩን የምንል ከሆን መሪነታችን ጥያቄ ሊነሳበት ይገባል፡፡
- ‹‹እርሱም፦ በዚያ ስፍራ ያሉት ከምርኮ የተረፉት ቅሬታዎች በታላቅ መከራና ስድብ አሉ የኢየሩሳሌምም ቅጥር ፈርሶአል፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋል አሉኝ። ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፥ አያሌ ቀንም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፡፡›› ***ነህ 1፡3-4፡፡***
- 

# መጽሐፈ ነህምያ - ክፍል ፩

- ‹‹ የሐካልያ ልጅ የነህምያ ቃል። በሀያኛው ዓመት በካሴሉ ወር እንዲህ ሆነ እኔ በሱሳ ግንብ ሳለሁ፥ ከወንድሞቼ አንዱ አናኒ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሰዎች ከይሁዳ መጡ እኔም የዳኑትን ከምርኮ የተረፉትን የአይሁድን ነገር የኢየሩሳሌምንም ነገር ጠየቅኋቸው። እርሱም፡- በዚያ ስፍራ ያሉት ከምርኮ የተረፉት ቅሬታዎች በታላቅ መከራና ስድብ አሉ የኢየሩሳሌምም ቅጥር ፈርሶአል፥ በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋል አሉኝ። ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፥ አያሌ ቀንም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፥ እንዲህም አልሁ። አቤቱ የሰማይ አምላክ ሆይ፥ ለሚወድዱህና ትእዛዝህን ለሚያደርጉ ቃል ኪዳንንና ምሕረትን የምትጠብቅ፥ ታላቅና የተፈራህ አምላክ ሆይ፥ እኔ ባሪያህ ዛሬ በፊትህ ስለ ባሪያዎችህ ስለ እስራኤል ልጆች ሌሊትና ቀን የምጸልየውን ጸሎት ትሰማ ዘንድ ጆሮህ ያድምጥ፥ ዓይኖችህም ይከፈቱ በአንተ ላይም ያደረግነውን የእስራኤልን ልጆች ኃጢአት እናዘዝልሃለሁ እኔና የአባቴም ቤት በድለናል። እኛም በአንተ ላይ እጅግ ክፉ ሠርተናል ለባሪያህም ለሙሴ ያዘዝኸውን ትእዛዝና ሥርዓት ሕግም አልጠበቅንም። አሁንም ብትተላለፉ በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ ወደ እኔ ብትመለሱ ግን ትእዛዜንም ብትጠብቁ ብታደርጓትም፥ ከእናንተ ሰዎች እስከ ሰማይ ዳርቻ ድረስ ምንም ቢበተኑ ከዚያ እሰበስባቸዋለሁ፥ ስሜም ይኖርበት ዘንድ ወደ መረጥሁት ስፍራ አመጣቸዋለሁ ብለህ ለባሪያህ ለሙሴ ያዘዝኸውን ቃል እባክህ አስብ። እነዚህም በታላቅ ኃይልህና በብርቱ እጅህ የተቤዥሃቸው ባሪያዎችህና ሕዝብህ ናቸው። ጌታ ሆይ፥ ጆሮህ የባሪያህን ጸሎት፥ ስምህንም ይፈሩ ዘንድ የሚወድዱትን፥ የባሪያዎችህን ጸሎት ያድምጥ ዛሬም ለባሪያህ አከናውንለት፥ በዚህም ሰው ፊት ምሕረትን ስጠው። እኔም ለንጉሡ ጠጅ አሳላፊው ነበርሁ።›› ***ነህ 1፡1፣ ነህ 1፡2፡፣ ነህ 1፡5-6፣ ነህ 1፡7፣ ነህ 1፡8-13፣ ዘዳግ 30፡፣1-ፍም ፡፡ ዘሌዋ 26፡1-ፍም፡፡***
- ‹‹ እግዚአብሔርም ሳሙኤልን አለው። እነሆ፥ የሰማውን ሁሉ ሁለቱ ጆሮቹ ጭው የሚያደርግ አንድ ነገርን በእስራኤል አደርጋለሁ። በዚያም ቀን በቤቱ ላይ የተናገርሁትን ሁሉ በዔሊ አወርዳለሁ እኔም ጀምሬ እፈጽምበታለሁ። ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ አውቆ አልከለከላቸውምና ስለ ኃጢአቱ በቤት ለዘላለም እንድፈርድ አስታውቄዋለሁ። ስለዚህም የዔሊ ቤት ኃጢአት በመሥዋዕትና በቍርባን ለዘላለም እንዳይሰረይለት ለዔሊ ቤት ምያለሁ። ሳሙኤልም እስኪነጋ ተኛ፥ ማልዶም ተነሥቶ የእግዚአብሔርን ቤት ደጅ ከፈተ። ሳሙኤልም ራእዩን ለዔሊ መንገር ፈራ። ዔሊም ሳሙኤልን ጠርቶ። ልጄ ሳሙኤል ሆይ፥ አለ እርሱም፡- እነሆኝ አለ። እርሱም፡- እግዚአብሔር የነገረህ ነገር ምንድር ነው? ከእኔ አትሸሽግ ከነገረህ ነገር ሁሉ የሸሸግኸኝ እንደ ሆነ እግዚአብሔር እንዲህ ያድርግብህ፥ እንዲህም ይጨምርብህ አለው። ሳሙኤልም ነገሩን ሁሉ ነገረው፥ አንዳችም አልሸሸገውም። ዔሊም። እርሱ እግዚአብሔር ነው ደስ ያሰኘውን ያድርግ አለ። ሳሙኤልም አደገ፥ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቀም ነበር። እስራኤልም ሁሉ ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ሳሙኤል ለእግዚአብሔር ነቢይ ይሆን ዘንድ የታመነ እንደ ሆነ አወቀ። እግዚአብሔርም ደግሞ በሴሎ ተገለጠ እግዚአብሔርም በእግዚአብሔር ቃል ለሳሙኤል በሴሎ ይገለጥ ነበር። የሳሙኤልም ቃል ለእስራኤል ሁሉ ደረሰ።›› ***ቀዳ ሳሙ 3፡11-21፡፡***

ይቆየን።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org